፳፪ ፡ ወምስ ፡ ዝኒ ፡ አስተዳሉ ፡ ሊተ ፡ ማኀደረ ።
ይህን ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ከዚህም ፡ ጋራ ፡ ሚቃ ፡ ሚቴ ፡ ሥራልኝ ፡ አለ ፡ ከመጣማ ፡ ብሎ ፡ ፈርቶ ፡ እንዲታረቀው ።

እስመ ፡ እትአወን ፡ በጸሎትክሙ ፡ ከመ ፡ ይሠርሐኒ ፡ እግዚአብሔር ።
በናንተ ፡ ጸሎት ፡ እግዚአብሔር ፡ ጐዳናዬን ፡ እንዲያቃናልኝ ።

ወይጸግወኒ ፡ ኪያክሙ ፡ (ፊል ፡ ፩ ፡ ፳፭ ።)
ጐዳናዬን ፡ አቅንቶ ፡ ከናንተ ፡ ጋራ ፡ እንዲያገናኘኝ ፡ እምናለሁና ።

፳፫ ፡ አምኀከ ፡ ኤጳፍራስ ፡ ዘተጼወወ ፡ ምስሌየ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ (ቈላ ፡ ፩ ፡ ፯ ፡ ፬ ፡ ፲፪ ።)
ከኔ ፡ ጋራ ፡ ከወደኔ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ያመነ ፡ ኤጳፍራስ ፡ ቸር ፡ አለህን ፡ ይላል ።

፳፬ ፡ ወማርቆስ ፡ ወአርስጥርኮስ ፡ ወዴማስ ፡ ወሉቃስ ፡ እለ ፡ ንኀብር ፡ ግብረ ። (ቈላ ፡ ፬ ፡ ፲ ፡ ፲፬ ።)
ማርቆስም ፡ እርስጥሮኮስ ፡ ዴማስ ፡ ሉቃስ ፡ ወንጌልን ፡ በማስተማር ፡ አንድ ፡ የምንሆን ፡ ቸር ፡ አለህን ፡ ይሉሃል ።

ወጸጋሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ምስለ ፡ መንፈስክሙ ።
የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋው ፡ ካድርባችሁ ፡ ይኑር ።

አሜን ፡ በውነት ።

ተፈጸመት ፤ መልእክት ፡ ኀበ ፡ ፊልሞና ፡ ወተጽሕፈት ፡ ኀሮሜ ፡ ወተፈነወት ፡ ምስለ ፡ አናሲሞስ ።
በሮም ፡ የተጻፈች ፡ በአናሲሞስ ፡ እጅ ፡ ለፊልሞና ፡ የተላከች ፡ ክታብ ፡ ደረሰች ፡ ተፈጸመች ።
ወ ስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ።

እንግሥቱ ፡ ላስጀመረን ፡ አስጀምሮ ፡ ላስጨረሰን ፡ ጌታ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ።

www.ethiopianorthodox.org